★ ዴሞክራሲያ ★

★

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞክራሲያ ቅጽ8፣ ቁጥር.2 ሚያዝያ 10/1973ዓ.ም

እየታገልን ሞተን፣ እየሞትንም ታግለን—
ወትሮም አሁንም በስተፊትም

አንድ ሕዝባዊ አብዮታዊ ትግል ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ ግቡን እስከ መታ ድረስ ብዙ ደንቃራዎችን፣ አያሌ ደርፎች በርካታ የሞት የሽረት ግብግቦች እንደሚገጥሙት የአብዮቶች ስንክሳር ያወሳናል::

ይህንንም ትግል የሚመራ አንድ አብዮታዊና ሕዝባዊ ድርጅትም፣ አንዴ እየጫጫ አንዴ ደግሞ እየፋፋ፣ እየከሳ፣ እየተንሰፋለ፣ እየሟላለት እየጎደለለት ድቀትና ትንሳኤ እየተፈራረቀበት፣ ከትንሽነት ወደ ትልቅነት፣ ከጠባብነት ወደ ሰፊነት እየተራመደ፣ እንደገናም ደግሞ እየተሸማቀቀ የተቃራኒ ክስተቶች በላዩ ላይ መፈራረቅ እያጋሰበት ግን ደግሞ መሰረቱን እያጠበቀለት፣ መከራን ችግርን ለመቋቋም የሚያስችል ጀግንነትና ቆራጥነት እየገነባ፣ ተመክሮ እያካበተ እያደገ እየጠነከረ የሚያስተማምን ይዘት ይቀዳጃል::

አንድ ድርጅት የሕዝባዊነትንና የአብዮታዊነትን ቀለም የሚቀዳጀው በጠላቶቹ ላይ ገንኖ ግርማ ሞገስ ለብሶ፣ መለከትና እምቢልታ የሚነፋለት፣ ዘፈን የሚገጠምለት፣ ሣር ቅጠሉ የሚያጨበጭብለት፣ ሁሉም ያበረከተው ድርሻ ትልቁ እንደሆነለት በሚገፋበት ጊዜ፣ የድል ጎዳና ግምጃ ተነጥፎ አደይ ወምሮ በሚጓዝበት፣ ዙሪያውን የሚያንቦገቡገው ፀሐይ ሁሉም ነገር ሞቅ ደምቆ በሚታይበት ሰዓት አይደለም::

ነባራዊ ሁኔታ ከሊቅ እንደ ወርግ ሲጫጫነው ከታች [illegible] [illegible] በንገው ሲደዙት፣ ከውጭም ከገቢም ቅራኔዎች ከበቢ ሲያደርጉት፣ ሲያፈገፍግ ሲያጠቃ ሲቆማ ሲቆስል ሲወግ፣ ሲያገግም፣ እንደገና ሲያመረቅዝርተ፣ ካሁንም ደግሞ ሲብስ እያስጨመ፣ ደዩውን እያስወገደ፣ ርስጠቱን እየከላ፣ ርትዑን እምነቱን ምርኩዝ አድርጎ መሥመሩን ሲያስደፍር ዝክንተሉን አራገፍ፣ የጠራና የጠጣለት ጊዜን ሸክፎ ሽንፍና ሰጠቅ ብሎ፣ ለአቸናፊነቱ ዋስትና የሚሰጠው ገምጋሚ አድርጎ፣ ከኅሁ ትቶ ጸሎቹ ከተጎከርው ተምሮ ቁርጠኛ ለመነሳት ባለው አብዮታዊ ድፍረትና ለ ክቢ ትግሉ አለበገሩነቱ ነው ሕዝባዊነቱና አብዮታዊነቱ ሊፈተን ሊለካ የሚቻለው::

ኢሕአፓም የምዝብሩን ሕዝብ ሰንደቅ ዓላማ አንግቦ የትግሉን ረጅም ጉዞ ሲጀምር ሌላ ስርጥ መንገድ አላጋጠመውም:: ሠፊው ምዝብር ሕዝብ ተነንግሮበስ ረጅምን በሉ በገዥ መደቦች በምዝበራ ኃይሎች ላይ አርዐድ አንቀጥቅጦ የከተተ ንቅናቄ ቢፈነዳበት ጊዜ ኢሕአፓም ገና በጨቅላነቱ በግንባር ቀደምነት የተሠለፈው ያካበተው ልምድ የወረሰው ተመክሮ ቀርስ ኖሮ ሳይሆን፣ የሚገጥመውን ውስብስብ ችግር ሁሉ ከሰፊው ሕዝብ ጋር አብሮ እየወደቀ እየተነሳ ለመቋቋም መራራ ዋጋን ጽዋ አብሮ ለመጨለጥ፣ በትግሉ ውስጥ እያደገ፣ ከትግሉ እየተማረ ዐቅም ጉልበት እያገኘ ወደፊት ለመራመድ በነበረው ቁርጠኛነት በመታገል ነበር::

ኢሕአፓ የሠፊው ጭቁን ሕዝብ ብሶትና ነፃነት በዚያች ቀውጢ ሰዓት አምጦ የወለደው እንደመሆኑ መጠን አይንፈሰብህ አይብ ነገብህ፣ አሸሩሩ ዳዴ ተብሎ ያሳደገው ባፈተተው ጊዜ ተጧሪ ትለት ታንቀሽ በሉ በከበከብ ለማደግ የታደለ አልነበረም:: "ቅኝና እሳት አቀረብሁልህ ወደ ፈቀድኸው እጅህን ስደድ" እንደ ተባለው ሕፃን ሁኔታ ከእሳቱ አደማስ ቢሻገር የምታበራው ወብ ዓለም የምትፈነጥቀው የትግል ጨራ ተመርቶ / ጋ ጎውነቱን —

ለነበልባሉ ዳርጉ ለመሻገር የደፈረ የቆረጠ ሕፃን እንጂ::–

ከዚህም ዘንድ የፊዩ ቡርዧው መንግሥት በሠፊው ሕዝብ ገሞራዊ ቁጣ እየተቀራረፈ ሲወድቅ በበድማው ላይ ማቆሚ ቆጥ የደመሯውን ፀኃደራዊ መንግሥት "አዚን ቅቡ እንጋቾነቱን በማጋለጥና ሥልጣን ወደ ሕዝባዊ ባለቤቷ ወደ ሠፊው ሕዝብ ሲተዛወር የጭርሰዱ አብዮታዊነትን የተጋጡ አርዮኛዎቹ፣ ሲያውል ሲያደርግ ቃሉ ን የቀለጠ እርምጃዎች ወደ እርገጫዎች እየተቀየሩ የከፋ ጭቆናና የጡስ ብዝበዛ እንደሚያስከትሉ በማስመለከትና በማታገል በከፈለው መስዋዕትነት በጭቁን ከፍተኛ ግፍ ኢሕአፓ ና ከትግሉ መድረክ ላይ ዱክ ዱክ ማለት አልደደመረ ሰፊውን ሕዝብ ከሊህቅ እስከ ደቂቅ አቀፍታል፣ ደግፍታል:: ሰፊው ሕዝብ ይህንን ምርጫ ሲያደርግ እርጥብ ከደረቅ ብሎ አይደለም፣ ኢሕአፓ ብቸኛ አማራጭ ነበር:: ቢንዳ ምህር ታደርግ ጋር ሰሞኛሞቹ፣ ሉደር ባይ ገራ ቀኝ ሲረግጥ፣ ምድረ ከላሽ ሸር ንዱ ሲል፣ በየጊዜው የሚፈጠረውን የፖለቲካ ውዝግብ እያጠራ፣ የሕዝቡን ትግል ደረጃ በደረጃ እየመራ ገሪው ኮከብ በመሆኑና የሷሉነቱንም በማያወላውል የደም ማህተም እያተመ በማስተላለፍ መሪነቱም አስተማሪ፣ ተሁት አገልጋይና ደግና ተጋዳይ በመሆኑም ነበር::

ስለዚህም ነው ፋሺስታዊ መንግሥት ተቀዳሚ ጠላት . . አድርጎ ያለ የሌለው . . ኃይሉን ያረባረበበት፣ ህልሙም ቅዠቱም እውኑም ኢሕአፓ የሆነበት:: ሆኖም እየተንቀለቀለ የመጣውን አብዮት ነበልባል ሊያቀዛቅዘው ቀርቶ ለብ ሊያደርገው እንኳን ከነዳት ሲርበተበት፣ አብዮት እሳት አደጋ አይነተኛ መከላከያ በመሆን ዓለም የመሰከረለትን ሶሺያል ኢምፔሪያሊዝምን ሙጥኝ በማለቱ ለጊዜውም ቢሆን ትንፋሹን ሊመልስ ችሏል::

የሶሺያል ኢምፔሪያሊዝም ኢትዮጵያ ውስጥ ጢልቃ መግባት በአብዮቱ ሂደት ላይ አንድ ትልቅ ሕምበር አኃደፉ አለ፤ ይህ ብርክ የያዘው ፋሺስታዊ መንግሥት፣ አነሆኝ ብሎ አኪት ሶሻያል ኢምፔሪያሊዝም እቅፍ ውስጥ በመግባቱ፣ ሰፊው ሕዝብ በመራራው ትግል እየተቀዳጃቸው የነበሩትን ድሎች መልሶ እየተነጠቀ፣ የፋሺስታዊ መንግሥት ፍጹም ስልጣን የሚያረጋግጡ የሶሺያል ኢምፔሪያሊዝምን አስትራቴጂያዊ ግቦች የሚያንፀባርቁ በኮሚቢ ጠበብት በተዮሩ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የሶሺያል ጉርና ውስጥ እንዲታጐር በመመንገዳ አፈሙዝ ተገደደ፣ የሀገራቱ ብሔራዊ ክብርና የበላይነት ተገፈፈ፣ የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲ ተነነ:: ሊቢደሮች፣ ተማሪ ምሁሮች፣ አርሶ አደሮች፣ አገር ወዳዶች የኮሚቢ ለዩ ለዩ የማሰቃያና ጢር– አርዙም አረመኔያዊ የተራቀቀ ጥበቦች መፈተኛ ሆኑ፤ ጥቂቶች ብሔሮች ተጨፈጨፉ፣ ተከታታይ ነጭ ሽብሮች የአብዮቱን ግንባር ቀደም ክፍል አጨዱት::

እንዲህ አይነቱም ደይን አብዮቱን የተጋፋኙት ብዙዎች፣ በሂደት ውስጥ በህሊና የሚገምቱት ቢሆንም ቅሉ፣ በገቢር ያንን የሚገፈንግ መራራ ጽዋ ጠፍ መንጋት ሲደመር፣ ተጨባጭ ሁኔታው ከበድ ያለ ለውጥ ቢያስመለከት የትግሉም ውስብስብነት ጐልቶ ሲታይ የድል ጉጉትም እየደበዘዙ ሲመጡ፣ የትግል መንፈሳቸው የሟሟ ቀኝ አደር ባይ አንጃዎች በኢሕአፓ ውስጥ ዱክ ዱክ በማለት ከፋሺስቱ መንግሥት ጋር ለመደራደርና የአብዮቱን አቅጣጫ ለማሣት ቁርጠው ተነሱ:: ቢሆቀትም የድርጅቱ የውጊን አሠራር በመጠቀም ለደርግ አድረው ከፍተኛ ጉዳት አደረሱበት:: ከውስጥና ከውጭ በተነዛረው በዚህ አዲሀሪ በትር በመሸማቀቁ፣ የኃይል ሚዛን ወደ ደርግ እያጋደለ በመሄዱ በመደናገጥ ሶሺያል ኢምፔሪያሊዝምን የማይገሰስ ኃይል አድርጉ በመቁጠሩ የተርበተበቱ ንቃተ ሕሊናቸው ዝቅ ያለ አባላትና፣ የአብዮቱ ጉዳና ከጠበቁት በላይ የሚያከትን ሆኖ ያገኙት ሁሉ አንገታቸውን እየደፉ በየምዕራፉ መነጠል ጀመሩ::

ከዚህም በላይ ሁሉ በተለያዩና በውስብስቡ የፖለቲካ ሁኔታዎች ቀስ በቀስ እያዘናጋ ያደገው የገራ አደር ባይ መስመርም ያስረፀው ቀኝነትና ከጠከር ማነስ የተንፀባረቀ አንዳንድ ድክመቶች ተነበብረው ሊያጠፍት ቢቃጡም፣ አሁንም በጽኑ እምነትና በቁራጥ ደግኖች መሪነት የተነነባ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ይህንንም ፈተና አለፍ፣ ድክመቱን